# ለቴዲ አፍሮ የልደት መወድስ

መልካም ልደት ይሁን እመኝልሀለሁ፣
ከቃሊቲ አውዚን መንጥቆ እንዲያወጣህ
የኢትዮጵያን አምላክ እማጸነዋለሁ።

ሀምሌ አራትን ያላወቃችሁ፣
በቴዲ አፍሮ ይሁንባችሁ።

አይዞህ ቴዲ አፍሮ ወጣቱ ጀግና፣
ወገብክን ሊሰብሩ ያዙህ ባፈና።
አንተ ግን ቆራጥ ከነ ስምህ፣
ያለፈን ታሪክ ህያው አርገህ፣
በላንቃ ቅላጼ ጨክ ብለህ፣
ውስጠ ዘላቂ ፍሬ ከናፍርህ።

አይዞህ ቴዲ አፍሮ ሆድህ እንዳይባባ፣
ሆነህ አንዳትቀር ወያኔ ሰለባ።
ሁሉም በልደትህ ቃል እየገባ
ትግሉን እንዲያጧጡፍ ሳይፈራ ሳይተባ።

አይዞህ ወገኔ የተመኘኸው ሌቱ ይነጋል፣
ዔሎሄ ሰምቶ ፍርዱን ይሰጣል።
አንተንም ካውዚን ይመነጥቃል።
የቃሊቲ አድባር ይጠብቅሀል፣
እመሀላችን ይገትርሀል።

ወሬ ባናበዛ ብሎናል መካሪ፣
ወይም ደሞ አስቃባጭ እመሀል ሰፋሪ።
መንጥቆ የሚያወጣ ከቃሊቲ ወህኒ፣
ሁላችን ባንድ ላይ አንድ ተአማኒ፣
መጨህ መጯጯህ ነው ላማ ሰበቅታኒ።

መልካም ልደትክን የምናከብረው፣
አንተን መንጥቀን ሰናሰወጣ ነው።
እስከዚያው ድረስ እግዜር ካንተ ጋ፣
ከኛም ትግላችን እስከምንተጋ።

**ክንፈ ሚካዔል**
**ሀምሌ 14 2ሺህ ዓ/ም**
**ሜልበርን፣ ኸታች ኸስር**